## ኦሮሞ ፓለቲካና የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እጣ ፋንታ

## በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ልብ ወለድ

## ክፍል ፯. ፪ የትም ወድቆ መቅረት፣ ካለፈው የቀጠለ

የእኛ ለእናቷ በህይወት መኖራቸውን እየተጠራጠረች "እናቴ በህይወት ካለሽ" ብላ ለእናቷ የማይላከውን ደብዳቤ ከፃፈች በኋላ ለአባቷ ለመፃፍ ደቂቃ አልወሰደባትም። የምትፅፈው ነገር ወደእነሱ ተልኮ እንደማይደርሳቸው ብታውቅም በጭንቅላቷ ውስጥ ያለውን ምስቅልቅል በፅሁፍ ማስፈሯን አልጠላችውም። አሁንም ማስታወሻዋን አወጣችና "የትም ወድቆ መቅረት " የሚል ርዕስ ሰጥታ ለአባቷ እንደሚከተለው መፃፍ ቀጠለች።

አባባ ውድ አባቴ እናቴን አስቀድሜ ለእሷ ስለፃፍኩ አንተ ስለእኔ ጉዳይ የእሷን ያህል አታስብም ብየ እንዳልሆነ ታውቀዋለህ። እሷ ብዙ ስለምትጨነቅ እኔና አንተ እሷ የማታውቀው የግላችን የቀደመ ሚስጥር ስላለንና አሁንም እኔ እማ ብትሰማ ይጎዳታል እንጅ አይጠቅማትም የምለው ብዙ ጉዳይ ስላለኝ ለአንተ ብቻ ለማካፈል ስለምፈልግ ነው።

በሆዴ ያለውን ሁሉ ላወጣው ሳስብ በየጊዜው አዳዲስ አስደንጋጭና አሳሳቢ ነገር ስለሚከሰት የቱን ይዤ የቱን እንደምተወው ግራ ይገባኛል። ሰሞኑን ደግሞ የበርሀ አምበጣ መንጋ ሰብል እያወደመ እንደሆነ፣ በዚህም ምክንያት ገበሬ በቂ ምርት ስለማያመርት ረሀብ ሊከሰት እንደሚችል ስሰማ ደግሞ በዚህ ኑሮ ላይ ርሀብ ይመጣ ይሆን የሚል ነገር ያሳስበኛል።

አሁን ደግሞ ጉምዞች ገለው የሰው ኩላሊትና ጉበት እየበሉ እንደሆነ እንደአዲስ አደባባይ እየወጣ ነው። አባባ የዛሬ 5 ዓመት በፍስለታ ፆም መጨረሻ ላይ እያለን፤ እኔም ገና ዩኒቨርስቲ ሳልገባ የሞረሽ ወገኔ የአማራ ድርጅት "በቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል፣ መተከል ዞን በሚኖሩ ዐማሮች ላይ የተፈፀመ የዘር ማጥፋት ወንጀል" በሚል ርዕስ  የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ወረዳዎችን በካርታ አስደግፎ **"ለመስማትም ሆነ ለማውራት ይዘገንናል!! በምን ቋንቋ እንግለጸው! ሰውን ሰው በላው! ጉምዞች ዐማሮችን አርደው በሏቸው!"** በሚል ያወጣውን የ88 ሰው መታረድ ዘግናኝ መግለጫ  አስተማሪየ ጎረቤታችን ከአዲስ አበባ ይዛው የመጣችውን ሰጥታኝ ሰጥቸህ ነበር።

ጉዳዩ አሳዛኝና የማይረሳ ስለሆነ እንደምታስታውሰው አልጠራጠርም። አንተም እንደሰጠሁህ ቶሎ አነበብከና በክብር ቆልፈህ አስቀመጥከው። እኔንም ልጀ መፀለይ ነው፤  ከፉ ጊዜ ላይ ነን፤  ጉምዝ ብቻውን አይዞህ ሳይባል ይህንን አያደርግም አልከኝ እንጅ እንደአንዳንዶቹ እንደዚህ አይነት ነገር አይደረግም አላልክም ነበርና እውነትነቱን ከፊትህ አንብቤ ተረድቸ ነበር። አንዳንድ ጊዜ አባቴ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ስለሆነ አምላክ እየረዳው ነገሮች ይገለፁለት ይሆን! ብየ አስባለሁ። ህዝቡን እግዚአብሔር ከመከራ ይጠብቀው።

ውድ አባቴ ህግና ፍትህ በሌለበት አገር ነፃነትን ማሰብ ሞኝነት ቢመስለኝም በእግዚአብሔር ተስፋ አይቆረጥምና እኛ ብናልፍ እንኳን ለታናናሾቻችን ነፃነት ያለበት ምድር እንዲያደርግልን የዘወትር ፀሎቴ ነው። አባባ እኛ የታፈንነው ተማሪዎች ነገር ያለቀለት ይመስለኛል። እንደውም ጓደኞች በህይወት ያሉ አይመስለኝም። ስለእነሱ ሳስብ ልቤ በጣም ይጨነቃል፣ አንዳንዶቹ በሞት አፋፍ ላይ እያሉ አይቻቸዋለሁ። ወላጆቻችን ሁሉ ልጆቻችሁ ሞተዋል ተብላችሁ እርማችሁን አውጥታችሁ ህይወታችሁ ከቆመበት ተነስቶ ቢቀጥል ምኞቴ ነው። እንደነአቶ ልደቱ አያሌው አይነት ታዋቂ ፓለቲከኞች

ፍርድ ቤት ነፃ ከለቀቃቸው በኋላ የኦሮሞ ፓሊስ ደጋግሞ አለቅም ብሎ ከህግ ተፃሮ መልሶ በሚያስርበት አገር ነፃ ወጥቸ፣ በሰላም ወደቤቴ ተመልሸ የሚል አጉል ተስፋም ጉጉትም የለኝም። እናንተም እኔን ትመጣለች ብላችሁ ባታስቡ እመርጣለሁ።

አባባ አንተ የምታውቀውን ቀድሜ ማገናዘብ ብችል ኑሮ ለዚህ መከራ አልዳረግም ነበር። አንድ ቀን ይሄ ትምህርት ቢቀርብሽ ብታቋርጭ ብለህ በጥሞና ስታናግረኝ እኔ አሻፈረኝ በማለቴ እማና የተቀረው ቤተሰብ ሰምተው እንዳይጨነቁ አስበህ ተይው ይቅር ብለህ ተውከው። በሚቀጥለው ቀን በወረዳ አስተዳደር በደል የደረሰባቸው አባባ አለሙ የህግ ተማሪ ስለሆነች ልጅህ ማመልከቻ ትፃፍልኝ በለውሻልና እርጃቸው ብለህ ከእሳቸው ጋር በቅድስት ስላሴ ቅጥር ግቢ ተቀጣጠርንና ተገናኘን።

የትም ወድቆ መቅረት፣ ይቀጥላል።

*ዘውዲቱ የማነ*

2020-10-09